# የአማራ ህዝብ የማይመጥን የወረደ የአማራ ፖለቲከኞች አካየድ፡-

መነኛውም ህዝብ የመጣበት የራሱ የሆነ ታሪካዊ ሂደት አለው። ሁሉም ህዝቦች እንደ ህዝብነታቸው የተከበሩ ናቸው። የሚያስከብርባቸውም፡ የራሳቸው ታሪካዊ ሂደት፡ ቋንቋ፣ ባህል፣ ስነ-ልቦናዊ ትስሳር …ወዘተ ያላቸው መሆናቸው ነው። አንድ ሰው በሰብአዊነቱ ከሌላ ሰው አይበልጥም አያንስምም። አንድ ህዝብም በህዝብነቱ ከሌላው አይበልጥም አያንሱም። ሁሉም የተፈጥሮ ሰው እኩል ነው። በተመሳሳይ ሁሉም ህዝቦች እኩል ናቸው። ጎደሎ የሆነ ሰውም ህዝብም የለም።

ሁሉም ሰው በአመለካከቱ፣ በታታሪነቱ፣ በችሎታው፣ በአስተዳደር ዘቤው፣ በስራ ፈጣሪነቱ …ወዘተ ግን አንድ ላይሆን ይችላል። በዚህ መመዘኛ ከሰው ሰው ልዩነት ኣለ። ይህ መመዘኛ እንዳለ በህዝቦችም ይሰራል። ሰው ከሰው ወይም ህዝብ ከህዝብ በአመለካከት፣ ብስራ ፈጣሪነት፣ በታታሪነት፣ በቋንቋ፣ በባህል፣ በመልክ ተለያየ ማለት ግን፡ በአፈጣጠሩም የተለያየ ነው ማለት አይደለም። የተፈጥሮ ሰውም ሰው ነው። ልኡላዊ ግዛት ያላቸው ህዝቦችና ህዝብና ናቸው። ከዚህ ውጭ ሌላ መጠርያም መመዘኛም የለውም።

በአለም ደረጃ ያሉ ሰባት አህጉሮች፡ በአህጉሮች ስር ያሉ የየራሳቸው የታወቀ ሕጋዊ መለያ ካርታ ያላቸው ልኡላዊ አገሮች፡ በአገሮች ስር ያሉ የክልል፡ የአውራጃ ወይም ዞን፡ የወረዳና የቀበሌ መስተዳድሮች፡ ሰው ለአስተዳደር አመችነት ሲል የፈጠራቸው እንጂ የተፈጥሮ ስጦታዎች አይደሉም። አህጉሮችና አገሮች፡ በዚህ መልክ የተሸነሸኑበት በጋራ ውሳኔና በፍቃደኝነት ነው ወይስ በተወሰኑ ኣካላት ፍላጎትና አስገዳጅነት የሚለውን ለታሪክ ትተን ኣለም በዚህ መልክ መሸንሸንዋ እንኳን ሆነ የሚያስብል ነው። ምኽንያቱ ለዚሁ በቢሊዮኖች የሚቆጠር ህዝብ እንደ አንድ ቀበሌ ነዋሪ ህዝብ ሁሉም በሰላም ለማስተዳደር አዳጋች ስለሚሆን ነው።

ማነኛውም ህዝብ የራሱ የሆነ የመጣበት ታሪካዊ ሂደትና መግለጫ እናዳለው ከላይ ገልጨዋለሁኝ። አሁን ያሉት ወደ 200 ገደማ የሚሆኑ ልኡላዊ አገሮችም የአሁኑ ቅርጻቸውና ልኡላውነት የያዙበት የየራሱ ታሪካዊ ሂደትና መገለጫ ኣለው። አንዲት ኣገር ልኡላዊት ኣገር ተብላ በአለም ማሕበረ-ሰብና የኣለም ማህበረ-ሰብን የሚወክለው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እውቅና ካገኘች፡ ትንሽም ትሁን ትልቅ፡ ድሃም ትሁን ሃብታም ልኡላዊ ግዛትዋን ከማወቅና ከማክበር ውጭ ሌላ ጤነኛ ኣማራጭ የለም።

እኛ ብዙ ህዝብ ያለን ትልቅ ኣገር ስለሆን በሌላ ትንሽ ኣገር ያለው የተፈጥሮ ሃብት በጉልበት የኛ እናደርጋለን የሚል አመለካከት፡ ከህግ አንጻር ህጋዊ ተቀባይነት የለውም። ከሰላም አንጻር ሰላም የሚሰጥ አይደለም። ከጥቅም አንጻርም የባሰ ጉዳት እንጂ ትርፍ አይገኝበትም። ግዛት የማስፋት እኩይ ህልም ለግዜው በህዝቦች መካከል ኣላስፈላጊ ጥላቻና ውድመት ይፈጥር እንደሆነ እንጂ፡ በስተመጨረሻ ሽንፈት መከናነቡ አይቀርም። የሩቅም የቅርብም ታሪክ የሚያስረዳንም ይህ ሃቅ ነው።

ግዛት መስፋፋት፡ የሰው ንብረትና ሃብት መቀማት የጥቂት ትምክህተኞችና የፖለቲካ ደላሎች ህልምና ፍላጎት እንጂ የህዝቦች እምነትና ኣላማ እንዳልሆነ ግን መታወቅ ኣለበት። በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ፡ የአክሱም ዘመነ መንግስት በዛጉዌ ዘመነ መንግስት መተካቱ፡ የዛጉዌ ዘመነ መንግስትን ብሃጻይ ይኩኖ ኣምላክ መተካቱ፡ ከሃጸይ ይኩኖ ኣምላክ ደርግ እስከ ወደቀበት ያለው የግዛት መስፋፋትና የጠሮነቶች አስከፊ ወቅት፡ በአማራ ገዥ መደቦች የበላይነት የተመራ መሆኑን የታሪክ ተመራማሪዎችና የታሪክ መዛግብት ይመስክራሉ። ይህ የግዛት መስፋፋትና የጦርነት አስከፊ ወቅት ባለ ቤት የአማራ ገዥ መደቦች እንጂ፡ በስማቸው የሚነገድባቸው የአማራ ጭቁን ህዝቦች ኣይደሉም። የአማራ ጭቁን ህዝብ እንዳሌሎች ጭቁን ህዝቦች ብስመ የግዛእት ኣንድነት ከጉዳት በስተቀር ጥቅም የማያገኝበት ክቡር ህይወቱን ሲገብር የነበረና ያለ ህዝብ ነው።

የአማራ ገዥ መደቦች በኢትዮጵያ ውስጥ ግዛታቸውን ለማስፋፋት የፈጸሙን ግፍ ለኢትዮጵያውያን ትቼ፡ እንደ ኣብዛኛዎቹ የአፍሪቃ፡ ኤስያና ላቲን ኣመሪካ ኣገሮች በጣልያን ቀኝ ገዥ ስር የነበረችና ከ 1890 ጀምሮ ከኢትዮጵያ፡ ሱዳን ጅቡቲ

የሚያዋስናት የመሬት ድንበር፡ እንዲሆም በቀይ ባሕር ከሚዋሰኑዋት ኣገሮች የባለ ቤት ግዛእትዋን የታወቀ ኤርትራ፡ እኛ ብዙ ህዝብና ታላቅ ኣገር፡ እነሱ ጥቂት ህዝብና ትንሽ ኣገር፡ እንዴት እነሱ የባህርና ወደቦች ባለ ቤት፡ እኛ ባህርና ወደብ ኣልባ እንሆናለን በሚል ገደብ የለሽ ስስታም ኣመለካካት፡ ኣቅም የገነቡ በመሰላቸው ወቅት ሁሉ፡ በኣገረ ኤርትራና ብኤርትራ ህዝቦች፡ የሸረቡት ሴራ፡ የጎሰሙን የጦርነት ነጋሪትና የፈጸሙን ጭካኔ የተሞላበት ግፍ የቅርብ ግዜ ትውስታ ነው።

የኣማራ ፖለቲከኞች፡ ታሪክን ኣዛብቶ በማቅረብ የተካኑ ናቸው። ፍትሓዊ ኣመለካከትና ተግባር ኣይጠጋቸውም እንጂ፡ ባገኙት መድረኽ ታሪክን ገልብጦ በመናገር ካልተደነቁ በስተቀር ኣይታሙም። ጭንቅላታቸው በግዛት መስፋፋት መልቶ፡ በምላሳቸው ስለ ሰላምና የህዝቦች ኣብሮነት ይሰብካሉ። በጭቁኑ የኣማራ ህዝብ እንየተመጻደቁ እኛኮ ከደሙ ንጹህ ነን ብለው ለማሳመን ይሞክራሉ። የሚያቀርቡት ሓሳብ ከሃቅ የራቀና የተዛባ በመሆኑ ግን፡ የኛ የሚሉትን የዋህ ህዝብ ከማጭበርበር ውጭ ለሌላው ማደናገር ኣይችሉም። ማንነታቸው በምላሳቸው ሳይሆን በተግባራቸው ለሚያውቀው፡ ብእጃቸው ለደማ፡ ለቆሰለና ወገኖቹን በግፍ በሞት ለተነጠቀ ህዝብ ማሳመን ከቶ ኣይቻላቸውም።

የኣማራ ፖለቲከኞች፡ ኤርትራ የኢትዮጵያ ኣካል ናት ብለው ነበር ኣይናቸውን ጨፍኖው ሲያጭበረብሩ የነበሩት። ኤርትራ በጣልያን ቀኝ ገዥ ስርና ብእንግሊዝ ሞግዚታዊ ወተሃደራዊ ኣስተዳደር ከ 50 ዓመት በላይ በባዕዳን ተገዝታለች። እነሱ ግን "በኣንድ ራስ ሁለት ምላስ" እንደሚባለው፡ ምንም ግብረገባዊም ሆነ ፖለቲካዊ ሃፈረት ሳይሰማቸው መኩራራት ሲፈልጉ በቀኝ ገዥዎች ኣልተገዛንም ይላሉ። በኤርትራ ስር ያሉ ወደቦች በጉልበት መውሰድ ሲፈልጉ ደግሞ ኤርትራ የኛ ናት ይላሉ። የሚገርም ነገር ነው።

ኢትዮጵያ ከኣፍሪቃ ለቀኝ ገዥዎች እጅዋን ያልሰጠች ( ያልተገዛች) ብቸኛ ኣፍሪቃዊት ኣገር ናት። ስለዚ ኢትዮጵያ የኣፍሪቃውያን ኩራት ናት ይላሉ። ይህ የተዛባ ታሪክ ነው ብቻ ሳይሆን እውነተኛ ማንነታቸው የሚያጋልጥ ጭብጥ ነው።

በዚህ በተዛባ ትርክታቸው ኤርትራ የኛ ናት ሲሉም፡ የኤርትራ ህዝብ የኛ ነው፡ ወገናችን ነው እያሉ ኣይደለም። እነሱ ኤርትራ የኛ ናት ሲሉ በግልጽ ቋንቋ በኤርትራ ልኡላዊ ግዛት ስር የሚገኝ ቀይ ባህርና ሁለቱም ወደቦች የባለቤት መብት ኣለን ነው እያሉ ያሉት። የኛ ነውና በሰላም ካልተመለሰ፡ በጉልበት እናስመልሰዋለን እያሉ ነው። በኤርትራ ልኡላውነት የሚገኝ ቀይ ባህርና ወደቦች የኤርትራ ህዝቦች ተፈጥሮኣዊ ሃብቶች መሆናቸው፡ የሰው መሆናቸው በፍጹም ሊቀበሉ ኣይፈልጉም። መነሻቸው እኛ 100 ሚሊዮን እነሱ 6 ሚሊዮን የሚል ደንቆሮ ኣመለካከት ነው። ግባቸውም ግዛት መስፋፋት ነው።ቀይ ባህር፡ ምስዋዕ እና ኣሰብ ወደቦች በጉልበት በሃይል የራሳቸው ንብረት ማድረግ፡ በኤርትራውያን የደም ጎርፍ ታላቅዋን ኢትዮጵያ ማበልጸግ የሚል የውሸት ትርክት ነው ያላቸው። ይህ ፍጹም መደበቅያ የሌለው በኣጉል እብሪት ያበጠ እኩይ የጦርነትና ውድመት ህልም ነው።

የኣማራ ታሪክ ጸሓፊዎች የድሮም የኣሁንም ፖለቲከኞችና በስነ-ኪነቱ ኣከባቢ ያሉ ኣንድ ኣንድ ሰዎች፡ ስለ ኤርትራ ቅድመ ጣልያን ቀኝ ገዥነትና ድህረ ጣልያን፣ ኤርትራ ሲገዛ የነበረ ጣልያንና ኢትዮጵያን ሲመራ የነበረ ሃጸይ ምልኒክ በኤርትራና ኢትዮጵያ ወሰን ኣከላለል ዙርያ ያደረጉትን ስምምነት፡ የስምምነት ሰነዶቹ የሚሉትን ትቶው ለራሳቸው በሚያመቻቸው መንገዲ ኣንዴ ሃጸይ ሚኒልክ እንዲህ ያሉት እንዲህ ማለታቸው ነው፡ እንደገናም ሃጸዩ ከጣልያን ጋር የተፈራረሙት ሃይል ኣጥቶው ተገደው ነው በማለት የራሳቸው የፈጠራ ታሪክ ጨምሮ ሲጽፉና ስያስተምሩ ይሰማሉ።

የኤርትራ ህዝቦች ፍቃደኝነት በሌለበት፡ በወቅቱ ኢትዮጵያ በእጃ ኣዙር ስትገዛ በነበረቹ ልዕለ ሃያልዋ ኣመሪካና ደጋፊዎችዋ፡ እንዲሁም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ግልጽ የሆነ ጫና የተፈጠረው ፈደሬሽን የተሰየመ የገዥዎች የፖለቲካ መጫዎቻ ሜዳ፡ በወቅቱ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስተር በነበረው ኣክሊሉ ሃብተወልድ፡ ፈደሬሽን መፍረስ የለበትም፡ ይፍረስ ከተባለም የኤርትራ ህዝብ በሪፈሬዶም ወይ ህዝበ ውሳኔ ድምጹን ሊሰጥበት ይገባል፡ ካልሆነ በሃይል ማፍረስ መዘዙ ከባድ ነው። በታሪክም፡ በህግም፡ በፖለቲካም ችግር ይፈጥራል ብሎ የተከራከረበትን ጉዳይ ሰሚ ኣጥቶ፡ የኤርትራ ህዝብ ሳይጠየቅ በማን ኣለብኝነት ብጉልበት የፈረሰበት ኣሳፋሪ ድርጊት፡ ኣውቆ እንዳለወቁ ሆኖ፡ ኤርትራ ወደ እናት ሃገርዋ ተመለሰች በሚል ተረት ተረት ሲዋሽ ቆይተዋል።

ከውጪው ኣለም የሚገናኙበትን የባህር በርና ንግድ የሚያስተላልፉበት ወደቦች እንጂ የህዝብ የባለቤትነት ጉዳይ ደንታ ኣልነበረባቸውምና፡ ፈደሬሽን ኣፍርሶ ኣንድነን ብሎ ሲዘምሩ ኣላፈሩም። ለኣገራዊ ነጻነቱና ማንነቱ ለ30 ዓመት ሲታገል የነበረ የኤርትራ ህዝብና፡ ጸረ-መደባዊና ብሄራዊ ጭቆና ሲታገሉ የነበሩ የኢትዮጵያ የኣርነት ንቅናቄዎች በጋራ ባካየዱት እልህ ኣስጨራሽ ትግል በ1991 ( 1983) ከኤርትራ መሬት የሃፍረት ካባ ለብሰው ተበታትነው በሃይል እስከ ወጡበት ግዜ፡ በኤርትራ ህዝብ ላይ የፈጸሙትን በደል፡ እነሱ በዳዮች ቢረሱት ተበዳዩ የኤርትራ ህዝብ ከቶውም የሚረሳው ኣደለም።

የኤርትራ ህዝብ ያ ሁሉ ስቃይ ኣልፎ ብ1993 የኣፍሪቃ ኣንድነት ድርጅት፡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ተወካዮችና ሌሎች ታዛቢዎች በተገኙበት ባካየደው ህዝበ ውሳኔ ልኡላውነቱን በህግ ኣረጋግጠዋል። የኣፍሪቃ ኣንድነትና የተባበሩት መንግስታት እውቅና ኣግኝቶ ኣካላቸው ሆኖዋል። በተባበሩት መንግስታት ስር ከሚገኙ ልኡላዊ ኣገራት ተቀላቅለዋል። ስለዚ ኤርትራ የኢትዮጵያ ኣካል ናት የሚለው የውሸት ትርክት ለኣንዴና ለመጨረሻ በፖለቲካም በህግም ተዘጋ። ኤርትራ የኣለም ማሕበረ-ሰብ የሚያውቃት ልኡላዊ ኣገር ናት። ኢትዮጵያም የዓለም ማሕበረ-ሰብ የሚያውቃት ልኡላዊ ሃገር ናት። ሁለቱም ልኡላዊ ኣገሮች ናቸው። ሁለት ህዝቦች ናቸው። የየራሳቸው የሚመሩበት ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች ያለቸው ነጻ ሃገሮች ናቸው።

ኣንድ ኣንድ የኣማራ የውሸት ታሪክ ደራሲዎችና፡ የጠራ ህዝባዊ ፖለቲካዊ ኣቋምና ተቋም የሌላቸው ፖለቲከኞች ግን ለም መሬት ላይ ተኝተው ኣስከ ኣሁን ከቀደምት ስህተታቸው ለመማር ፍቃደኞች ኣይደሉም። ኣሁንም ብኣካል ተሸነፍን እንጂ የግዛት መስፋፋት ህልማችን ኣልሞተም እንዳሉ ናቸው። የኤርትራ ወደቦች በእጃችን እስክናስገባ ድረስ መቸም ቢሆን በሰላም ኣንተኛም፡ ኣናስተኛም እያሉ ነው። የሚገርም የኣቋም ልፍስፍነት፡ የሚገርም የፖለቲካ እብደት ነው። የኤርትራ ህዝብ ቁጥር ጥቂት ኣገሪትዋም ትንሽ ስለሆነች፡ በሃይል ወረን ባህሩና ወደቦቹ የኛ እናደርገዋለን። ለምን እኛ በኣፍሪቃ ቀንድ ብዙ ህዝብ ነን። ያለ ቀይ ባህርና ወደብ መኖር ኣንችልም ይላሉ። ሸኽ ሑሴን ዓላሙዲ ኣንድ ሰው ናቸው። ግን በቢሊዮን የሚቆጠር ሃብት ያላቸው ቱጃር፡ ከወደ ኣማራ ፖለቲከኞች እየተሰማ ያለው ኣመለካከት፡ ብዙ ድሃዎች ባሉባት ኣገር ኣንድ ሰው ይህን ያህል ሃብት መያዝ የለበትም፡ ድሆች ንብረቱን ዘርፈው መውሰድ ኣለባቸው እንደማለት ነው። ህዝባዊ ፖለቲከዊ ኣቋም የራቀው፡ ህግ የማይገዛው ሁሉም ለኔ በሁሉም እኔ ኣይን ያወጣ የማይታረም እብደት።

ይህ የጦርነትና ግዛት የማስፋፋት ጸረ-ህዝብ ህልም በተለይ፡ የኢህኣደግ ስራ ስፈጻሚ ኮሚቴ የኤርትራና የኢትዮጵያ እልባት ያላገኘው የድንበር ጉዳይ፡ ያለ ቅድመ ሁኔታ የድንበር ኮሚሽኑ በዘሄግ ብሳለፈው ውሳኔ መሰረት ተቀብለን እንፈጽማለት ባለበት፡ ኣምባገነኑ የኤርትራ መሪም በሰነ 20/2018 በተከበረው የሰማእታት ቀን፡ የኢህኣደግ ውሳኔና ጥሪ እቀበለዋለሁ የሚል መግለጫ በሰጠበትና፡ በሁለቱም ህዝቦች ግልጽነት የሌለበት ተብሎ የሚነቀፍው፡ የሁለቱም መንግስታት ሳይሆን የሁለት ሰዎች ንግግር ተደረገ ከተባለ በውሃላ በከፋ መልኩ ብሶበታል። የፖለቲካ እብደቱን የከፋ ያደረገው፡ የኤርትራ ህዝብ በስደት ተበታትነዋ፡ በድህነት ላሸቀዋል። ከድሮም በኤርትራ ነጻነት የጸና ኣቋም ያልነበረው፡ በኢትዮጵያ ኣንድነት የሚያምነው ፕረዚደንት ኢሳያስ ኣፈወርቂ ይዘን የመጨረሻ እድላችን የምናይበት ግዜ ኣሁን ነው የሚል መረን የለቀቀ መመዛኛ ነው። ለዚህም በገሃድም ብስውርም እየተንቀሳቀሱበት ነው።

ከኣምባገኑን መሪ ኢሳያስ ሙሉ መተማመኛ እደተሰጣቸውም ይናገራሉ። ትላንትም ዛሬም የህዝቦች ነጻነትና መብት ጨፍልቆ ያራሱን ሃገራዊ ጥቅም ለማረጋገጥ፡ ምስራቅ ኣፍሪቃን በብቸይኝነት ለመቆጣጠር እጁን ሲያስገባ የነበረው የኣመሪካ መንግስትም ኣይዞቹ ግፉበት፡ ስጋት ኣይግባቹ እኔ ኣለሁላቹ የሚል መተማመኛ እንደ ሰጣቸውም ይናገራሉ። ኢሳያስ ጎንደር ባህር-ዳር ሄደዋል። የኣማራ ፖለቲከኞችም ኣስመራ ተመላልሰዋል። በኢትዮጵያ የሚገኘው የኢሳያስ ኣምባሳደርም በ2012 የጥምቀት በኣል በጎንደር ከተማ ተገኝተዋል። ከ 50 ዓመት በውሃላ በጎንደር መገኘቱ የተሰማው ልዩ ደስታ ገልጸዋል። እንደ ማነኛውም ሰው ከኣንድ ወደ ሌላ ቦታ መሄዳቸው ዝምድናን መፍጠራቸው ነውርነት የለውም። ከታሪካቸውና ከተጨባጭ ሁኔታቸው ኣንጻር ሲታይ ግን ለምን ዓላማ የሚል ጥያቄ ያስነሳል። የሰው ንብረት የራሳቸው ለማድረግ ላይ ታች እያሉ ያሉት ኣስፋ ወሰኖች፡ የኢሳያስን ኣምባሳደር የኢትዮጵያ ኣንድነት ምልክት ብሎ የሚገልጹትን

የድሮ ሰነደቅ ዓላማ ኣልብሶ፡ የኤርትራ ካርታ፡ ከኢትዮጵያ ካርታ ኣገናኝቶው የህውና እይሉን ስሙልን ድላችን ሲሉ ተሰምተዋል። እንደዛ ሲያደርጉ ምንም ሃፈረት ኣልተሰማቸውም።

በተሳሳተ ታሪኽና የኣመሪካን ኣይዞባይነት (ደጀን) ተደግፎ 30 ዓመት ተዋግተው፡ የድሃው የኢትዮጵያ ህዝብ ልጆችና ሃብት ገብረው ባዶ እጃቸው መዋጣታቸው ረስተውታል። በቀለል የማይለቅ መጥፎ ባህሪ የሚባላው እንዲህ ዓይነት ነው። የኤርትራ ህዝብ ሃገራዊ ስሜት፡ የኣላማ ጽናትና ቆራጥነት የሞተ መስለዋቸዋል። የሚገርምም የሚያሳፍርም ካለፈው ውድቀቱ የማይማር የወረዳ ጦረኛ ባህሪ።

ከዚህ ርእስ ጋር ሳልወጣ የኣሁኑ የኣማራ ገዥ ፓርት ፖለቲከኞች የፈጸሙት፡ ለተከበረው የኣማራ ህዝብ ኣንገት የሚያስደፋ ሌላ ኣሳፋሪ ተግባር ልግለጽ። ለታጋይ በረከት ስምኦን የኤርትራውነት ዘር ሃረጉን ቆጥሮ የኣማራ ህዝብ ጥቅም ኣሳልፎ የሰጠ ጠላት ብለው ወንጅለውታል። የሚገርም ነገር ነው። ታጋይ በረከት ስምኦን ጎንደር ተወልዶ፡ ጎንደር ኣድጎ፡ ጎንደር የተማረና፡ ከጎደር ጓደኞቹ ለጭቁን ህዝቦች መብትና እኩልነት መከበር ከኢህኣፓ ጀምሮ፡ ኢህዴን በኣደን የታገለና በኣገር ደረጃም ሚኒስተር ሆኖ የሰራ በፖለቲካዊ ብቃቱ፡ የዓላማ ጽናቱና ህዝባዊ ወገንተኝነቱ የታወቀ ፖለቲከኛ መሆኑ ይታወቃል። ታጋይ በረከት በፖለቲካዊ ኣቅሙና ህዝባዊ ወገንተኝነቱ ስለ በለጣቸው ግን፡ ኤርትራዊ የዘር ሃረግ እንደ ወንጀል ወስደው "ኣቶ በረከት ማን መሆኑ ይታወቃል" እያሉ ስሙን በማጥፋት በሙስና ወንጅለው በእስር እያሰቃዩት ይገኛሉ። በእወነት እንነጋገር ከተባህለ ታጋይ በረከት ስምኦን ጎንደሬ ኢትዮጵያዊ እንጂ ኤርትራዊ ኣይደለም። ወላጆቹ ግን በርግጥ ኤርትራውያን ናቸው። የበረከት ትውልድ፡ እድገትና ስራ ግን፡ ኢትዮጵያዊም ለኢትዮጵያም እንጂ ኤርትራዊ ኣይስብለውም። እነዚህ የስልጣን ጥመኞች ግን ፖለቲካ መላ ቅጡ ሲጠፋቸው ኤርትራዊ የዘር ሃረጉን ቆጥሮው "በረከት ማን መሆኑ ይታወቃል" በማለት ስሙ እንዲጠፋ ሰርተዋል። በሙስናም ወንጅለው ኣስረውታል።

ታጋይ በረከት በያዘው ፖለቲካዊ ኣቋም ያለው የማይደራደር ጽኑ ስብኣና ካልሆነ በሙስና የሚታማ ሰው ኣይደለም። በስመ ኣማራ ህዝብ የሚያጭበረብሩ የስልጣን ጥመኞች የኣዴፓ ፖለቲከኞች ግን ከስልጣን ለማስወገድና መልካም ስሙም እንዲጠፋ የወደቀና የዘቀጣ ሃላ ቀር ዘመቻ ከፍተውበታል። በረከት ስምኦን ኣማራ ጠል ነው፡ የኣማራ ህዝብ ጥቅም ኣሳልፎ ሰጥታዋል። በሙስናም ተዘፍቀዋል በተራ ጥላቻና ዘረኛ ኣመለካከታቸው መንጋ ነብሰ ገዳዮች ኣሰማርቶው በማርቆስ ሊያስገድሉት ሞክሮው ነበር። ይህ ኣልሳካ ሲላቸው፡ የጥረት ኮርፖሬሽን የቦርድ ኣባል በነበረበት ግዜ ከነ ታጋይ ታደሳ ካሳ (ጥንቅሽ) ሙሳና ፈጽመዋል ብለው በተቀነባበረ ሴራ እያሰቃዩት ይገኛሉ።

በዚህ ላይ የኣማራ ጸረ-ሙስና ኮሚሽን ሊቀ መንበር በረከትና ታደሰ የታሰሩበትን ምኽንያት ኣስመልክቶ በዕለቱ በኣማራ ቴሌቪዥን የሰጡት መግለጫ እንዲህ የሚል ነበር። ኣንደኛ፡ እነዚህ ሰዎች የሃሳብ ኣመንጪ በመሆናቸው። ሁለተኛ ህዝቡ ብኣዴን ፈሪ ነው፡ ደካማ ነው ስለሚለን ደካማና ፈሪ ኣለመሆናችን ለማረጋገጥ የወሰድነው እርምጃ ነው የሚል ነበር። የበለጠ ለማራጋገጥ የሚፈልግ ሰው እነ በረከት ያተሰሩበት ቀን በኣማራ ቴለቭዥን የተሰጠ መግለጫ ፈልጎ ማግኘት ይችላል። ይህ በየተኛውም መመዘኛ ለሰዎች መወንጀያ ምኽንያት ሊሆን ኣይችልም። የዚህ ዋና ምኽንያት ፖለቲካዊ ክሽፈት ነው። ዘረኝነት ነው።

ከሁሉም የሚገርመው በበረከት በኩል የሚመጣ ኤርትራዊነት "በረከት ማን መሆኑ ይታወቀል" እየተባለ በኣማራ ህዝብ ጠላትነት ይፈረጃል። በገዳዩና ኣፍረሹ ኢሳያስ ኣፈወርቅ መስመር የሚመጣ ኤርትራውነት ደግሞ እንደ ወዳች ተወስዶ ያለ የሌለ የተዛባ ታሪክ ይለፈፍበታል። ለበረከት ስምኦን በኤርትራዊነቱ የሚጠላ የሚወነጅል ኣስሮ የሚያሰቃይ፡ የኤርትራ ህዝብ ጠላት ለሆነው ኢሳያስ ወዳች ነኝ የሚል የኤርትራ ህዝብ ወደች ሊሆን ኣይችልም። የበረከትን የዘር ሃረግ ጠልቶ፡ የኢሳያስ ኤርትራውነት የተወደደበት ምኽንያት ምስጢሩ ግልጽ ነው። " እንኳን ሲሸጡን ሲስማሙብን እናውቃለን" ነው ነገሩ።

በመጨረሻ ማለት የምፈልገው፡ የኣማራ ህዝብ እንደ ህዝብ ትላንትም ዛሬም የኤርትራ ህዝብ ወዳች እንጂ ጠላት ኣለመሆኑን ነው። ለወዲፊቱም የኤርትራ ህዝብ ጠላት ኣይሆንም። በኣማራ ህዝብ ተወልዶ ኣድጎ ለኣማራ ህዝብ ፍትህ እኩልነት

ደሞክራስያዊ ኣንድነት እድገት ዕድሜ ልኩ ሲሰራ የቆየው ነባርና እውቅ ፖለቲከኛ ታጋይ በረከት ስምኦን የኣማራ ህዝብ ጠላት ኣይደለም። በሱና ባልደረቦቹ የተፈጸመው የዘረኝነት ጥቃት ይቁም። በሴራ ከታሰረበት የፈታ የሚል የኣማራ ህዝብ በሰላማዊ ሰልፍም ጭምር ድምጹን ሊያሰማበት የገባል። የኣማራ ደሞክራት ምሁራንና የህግ ባለመያዎም ለህልናቸውና ለህዝባችው ክብር ሲሉ ተመሳሳይ ኣቋም በመያዝ ድምጻቸው ሊያሰሙ ሊከራከሩለት ይገባል የሚል እምነት ኣለኝ። ካልሆነ ግን በረከት ስምኦን በኤርትራዊ የዘር ሃረጉ ኣስሮ የኤርትራ ህዝብ እወዳለሁ ማለት ቀልድ መሆኑን መረዳት ጥሩ ነው የሚል ሓሳብ ኣለኝ።

ኣብራሃ ታደሰ ነኝ ከኣማራ ክልል ባህር-ዳር

20-01-2020